## ትምህርት 11

### ጥምቀት ምንድነው?

አንድ ሰው በጌታ ኢየሱስ በማመን ከዳነ በኋላ ማከናወን ከሚያስፈልጉት ስርዓቶች አንዱ የውሃ ጥምቀት ነው፡፡

**በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሰፈሩ ዋናዎቹ የጥምቀት ዓይነቶች**

1. **የመጥምቁ ዮሐንስ - የውሃ ጥምቀት/የንስሃ ጥምቀት**

በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የመጀመሪያው በውሀ ያጠመቀ ሰው መጥምቁ ዮሐንስ ነበር፡፡ ይህም ያደርግ የነበረው ያልዳኑና የተለያየ ኃጢአት ያደረጉ እስራኤላዊያን ንስሃ በመግባት ኃጢአት ማድረግን ትተው በልባቸው አዳኙ ጌታ ኢየሱስን ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው መሲሁ እንደሆነ አምነው መቀበል እንዲችሉ የሚያመቻች ነበር፡፡ ይህ ጥምቀት የልባቸው የውስጥ ንሰሃ ውጫዊ ማሳያና በእግዚአብሔር መንገድ ለመሄድ ፈቃደኛ በመሆን የተለዩትን የሚያሳይ መግለጫ ነበር፡፡

*ማቴ 3፡1-6፣ በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። [2] ስብከቱም፣ “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ” የሚል ነበር።...[5] ከኢየሩሳሌም፣ ከመላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ዙሪያ ካለው አገር ሁሉ ሰዎች ወደ ዮሐንስ ይጐርፉ፣ [6] ኀጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር።*

*ማር 1:4-5, ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ። [5] የይሁዳም አገር ሁሉ የኢየሩሳሌምም ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፥ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር።*

መጥምቁ ዮሐንስ እስራኤላዊያን ስለ ኃጢአታቸው ንስሃ እንዲገቡ በማድረግ የማጥመቅ አገልግሎት ያከናውን የነበረው ጊዜው ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን የሽግግር ሂደት የጀመረበት ወቅት ስለ ነበር ነው፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነብይ በመባል ይታወቃል፡፡ ሄሮድስ የልደቱን ቀን በሚያከብርበት ዕለት በእስር ቤት የነበረው መጥምቁ ዮሐንስ፣ ራሱን አስቆርጦት በመሞቱ፣ የንስሃ ጥምቀት ማከናወኑም አበቃ፡፡ እንኳንስ በአሁኑ ጊዜ የንስሃ ጥምቀት ማካሄድ ቀርቶ ከመጥምቁ ዮሐንስ ሞት በኋላ በእስራኤል ውስጥ እንኳ በእርሱ ፈንታ ተተክቶ የንስሃ ጥምቀት በማጥመቅ የቀጠለ ሰው ስለመኖሩ በመጥሐፍ ቅዱስ የሰፈረ አንድም ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ የዚህ ዓይነቱ የንስሃ ጥምቀት በአሁኑ ጊዜ በጌታ ኢየሱስ አምነው በዳኑ ምዕመናን የመከናወን አስፈላጊነትም ሆነ ጠቀሜታ የለውም፡፡

ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን የፋሲካ ራት ከሐዋሪያቱ ጋር እየተመገቡ ሳሉ፣ ጌታን ሊገድሉ ያሴሩ የአይሁድ ሀይማኖት መሪዎች ይዘው ሊገድሉት ከጥቂት ሰዓታት በኋላ እንደሚመጡ አውቆ የእርሱ ስጋና ደም የመውሰድ ስርዓት መሰረተ፡፡ አዲስ ኪዳን የተጀመረው ጌታ አየሱስ አገልግሎት በጀመረበት ጊዜ ሳይሆን ስለኃጢአታችን ስርየት፣ መስቀል ላይ ሕይወቱን መስዋዕት አድርጎ በሰጠበት ደሙን ስለኛ ኃጢአት ስርየት ባፈሰሰበት ሰዓት ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጥቶ ለኛ ኃጢአት መስዋዕት በመሆን ደሙን ስላፈሰሰልንና ሕይወቱን ስለኛ መስዋዕት አድርጎ ስላቀረበ የኃጢአታችን ማስተሰሪያ፣ ከንስሃ ጥምቀት የላቀ ታላቅ ዋጋ ያለውና ከሁሉም ኃጢአት ማንጻት የሚችል የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደ ፈሰሰልን መጽሐፍ ቅዱስ አበክሮ ያስረዳል፡፡

የዮሐንስ ጥምቀት ከሃጢአት የማንጻት ተግባሩ አዲስ ኪዳን እንደ ተጀመረ ማብቃቱን ከሚያሳዩ ብዙ ጥቅሶች ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው፡፡

*ማቴ 26፡27-28፣ ከዚያም ጽዋውን አንሥቶ አመሰገነ፤ ለደቀ መዛሙርቱም በመስጠት እንዲህ አላቸው፤ “ሁላችሁም ከዚህ ጠጡ፤ [28] ስለ ብዙዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።*

*1 ዮሐ 1፥7፣ “… የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።”*

2. **የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡-**

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሁሉም አማኞች የሚያካትትና የሚፈጸመውም እያንዳንዱ አማኝ በሚድንበት ቅጽበት ነው፡፡ ይህ ጥምቀት እያንዳንዱ ክርስቲያን ከክርስቶስ አየሱስ ጋርና አንዱ አማኝ ከሌላው አማኝ ጋር ኅብረት የሚያደርግበት/የሚገናኝበት/የአንድ አካል ክፍል የሚሆንበት ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የማይደጋገም አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ነው፡፡ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ በጴንጠቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ በሐዋሪያት ላይ በወረደበት ጊዜ ተከናውኗል፡፡ ሐሥ 2፡1-4፣

በአዲስ ኪዳን 2ኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መከናወኑን የሚያሳየው ጥቅስ ሐሥ 11፡15-16 ነው፡፡

3ኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መከናወኑን የሚያመለክተው ጥቅስ ደግሞ 1ቆሮ 12፡13 ላይ ያለው ነው፡፡ ሌሎቹ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደፊት እንደሚከናወን የሚናገሩ አንጂ አንደ ተከናወነ የሚያሳዩ ተጨማሪ ጥቅሶች የሉም፡፡

*1 ቆሮ 12፡12-13፣ አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም አንድ አካል ነው፤ ነገር ግን ብልቶች ብዙ ቢሆኑም አካል አንድ ነው። ክርስቶስም እንደዚሁ ነው። [13] አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል። (ይሄ ጥቅስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ነው የሚያሳየው፡፡)*

*ማቴ 3፥11፣ “እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን ጫማውን መሸከም የማይገባኝ፣ ከእኔ የሚበልጥ ኀያል ከእኔ በኋላ ይመጣል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል።” (ሉቃ 3፡ 16፣ ማር 1፡8)*

3. **በጌታ ኢየሱስና በሐዋሪያቱ የተከናወነ - የውሃ ጥምቀት**

3.1) **የውሃ ጥምቀት አንድ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ አማኝ መላ ሰውነቱን በውሃ ውስጥ በማጥለቅ እንዲሸፈን አድርጎ ወዲያውኑ መልሶ ከውሃው በማውጣት የሚከናወን ነው፡፡** "ባፕቲድዞ" የሚለው የግሪክ ቃል መላ ሰውነትን ሙሉ በሙሉ በውሃ ውስጥ መንከርን የሚያመለክት ስለሆነ ትክክለኛው የውሃ ጥምቀት በውሃ ውስጥ በማጥለቅ ነው እንጂ በመርጨት የሚከናወን መሆኑን አያሳይም፡፡ አንድን ሰው በውሃ ውስጥ ማጥለቁ ከጌታ ጋር ሞቶ በመቀበር እንደ ተባበረ፣ ከውሃ ውስጥ መልሶ መውጣቱ ደግሞ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር እንደ ተነሳ መቁጠሩን ማሳያ ነው፡፡

*ሮሜ 6:3-5, ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንድንሆን የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? [4] ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ፣ እኛም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንኖር በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል። [5] በሞቱ ከእርሱ ጋር እንደዚህ ከተባበርን፣ በትንሣኤው ደግሞ በርግጥ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን። (1 ጴጥ 2፡24፣ ቆላ 2፥12)*

*ሮሜ 6፡8-11፣ ከክርስቶስ ጋር ከሞትን፣ ከእርሱ ጋር እንደምንኖር እናምናለን። [9] ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶአልና፣ ዳግመኛ እንደማይሞት እናውቃለንና፤ ሞት ከእንግዲህ በእርሱ ላይ ጕልበት አይኖረውም።*

*[10] በሞት ጊዜ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለኀጢአት ሞቶአል፤ ነገር ግን በሕይወት መኖርን ለእግዚአብሔር ይኖራል። [11] እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ።*

በአውሮፓና በመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ሁለት ጓደኞች ወይም ፍቅረኞች በሆነ ጉዳይ አምርረው ተጣልተው ሲለያዩ፣ ከእንግዲህ ወዲያ ተመልሰው በመታረቅ ምንም ዓይነት ሕብረት እንደ ማያደርጉ ለማረጋገጫ "እንደሞትኩ ቁጠረኝ" በመባባል መለያየት የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ለማድረግ ተጠመቅን ማለት ከኃጢአት ጋር ዳግመኛ ላንተባበር/ላንገኛኝ/ላንነካካ ቁርጠኛ ውሳኔ አድርገን እንደ ተለየየን እንቆጥራለን ወይም እንወስናለን ማለት ነው፡፡

(ዮሐ 4፡1-2፣ *ፈሪሳውያን ከዮሐንስ ይልቅ ኢየሱስ ብዙ ደቀ መዛሙርትን እንዳፈራና እንዳጠመቀ ሰሙ፤ [2] ዳሩ ግን ያጠመቀው ኢየሱስ ሳይሆን ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ።*) ይሄ በተራ ቁ. 3 ላይ የተጠቀሰው ጌታ ኢየሱስ ራሱ እንዳላጠመቀ ለማሳየት ሲባል የተጨመረ ነው፡፡

3.2) **የውሃ ጥምቀት ለአሮጌው በኃጢአትና አለማዊ ምኞት ለተበከለ ሕይወት ከክርስቶስ ጋር በመሞት መተባበርንና በአዲስ ሁኔታ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቃል፣ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ አኳኋን ለመኖር ከክርስቶስ ጋር የመነሳት ውስጣዊ ለውጥ፣ ውጫዊ መገለጫ (ሲምቦል) ነው**፡፡ ስለዚህ አንድ አማኝ በውሃ ከተጠመቀ በኋላ ራሱን ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ሞቶ እንደ ተቀበረና ከጌታ ትንሳኤም ጋር አብሮ የተለወጠ ሕይወት ለመኖር እንደ ተነሳ በመቁጠር በጽድቅ ሕይወት የሚመላለስ ከሆነ ጌታውን በመታዘዝ አከበረ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን የቀድሞ ኃጢአቱን ደጋግሞ ማድረግ ከቀጠለ በጌታ አምናለሁ ማለቱም ሆነ መጠመቁ ለይምሰል ያህል የተደረገ እንጂ ውስጣዊ ለውጥ እንዳላስከተለ ማሳያ ነው፡፡

3.3) **ይህ ጥምቀት የሚከናወነው በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም ነው**፡፡ ይህም ሕብረታችን ከእግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ጋር መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ *ማቴ 28፡19-20፣ "ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ [20] ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"*

3.4) ከዚህ በላይ የሰፈረው ማቴ 28፡19-20 ጥቅስ የውሃ ጥምቀት፣ **ጌታ ኢየሱስ ራሱ ያዘዘው ትዕዛዝና የመሰረተው ሥርዓት መሆኑን** እንጂ በሰው የተመሰረተ አለመሆኑን ስለሚያስረዳ ማንኛውም የጌታ ኢየሱስ ተከታይ ሳይጠመቅ ሊተወው የሚቻል አይደለም፡፡ *መጠመቅ የጌታን ትዕዛዝ ተቀብሎ መታዘዝን ያሳያል፤*

3.5) **ማንኛውም ሰው በዚህ ስም ለመጠመቅ ማሟላት ያለበት መስፈርቶች፡-**

ሀ) ኃጢአተኛ መሆኑን አውቆ በሰራው ኃጢአት ተጸጽቶ ንስሃ መግባት የሚችል፣ ለ) የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና አስተምህሮ ሰምቶ መማር የሚችል፤ ሐ) የሰማውን የጌታ ኢየሱስ ማዳን ስራ ቃል በልቡ ማመን የሚችል፣ መ) ኃጢአት ማድረግን ትቶ በቅድስና ለመኖር በመምረጥ የጌታ ኢየሱስ ደቀ-መዝሙር ለመሆን መወሰን ወደ ሚያስችል የዕድሜ ክልል የደረሰ፤ ሠ) የጌታ ኢየሱስ አዳኝነት በአፉ መመስከር የሚችል መሆን አለበት፡፡ እነዚህን መስፈርቶች የማያሟሉትን ማጥመቅ ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር አግባብነት የለውም፡፡

> *ማር 16፡15-16፣ እንዲህም አላቸው፤ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ [16] ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።"*
> *ዮሐ 11፡25-27፣ ኢየሱስም፦ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤*

*[26] ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት። [27] እርስዋም፦ አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው።*

*ሐሥ 8፡34-38፣ ጃንደረባውም መልሶ ፊልጶስን፣ "ነቢዩ ይህን የሚናገረው ስለ ማን ነው? ስለ ራሱ ነው፣ ወይስ ስለ ሌላ ሰው? እባክህ ንገረኝ" አለው። [35] ፊልጶስም አፉን ከፈተ፤ ከዚሁም መጽሐፍ ክፍል ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት። [36] በመንዝ ላይ ሳሉም ውሃ ካለበት ስፍራ ደረሱ፤ ጃንደረባውም፣ "እነሆ፣ ውሃ እዚህ አለ፤ ታዲያ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምን ነገር አለ?" አለው። [37] ፊልጶስም፣ "በፍጹም ልብህ ካመንህ መጠመቅ ትችላለህ" አለው። ጃንደረባውም፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" ሲል መለሰለት፤ [38] ሠረገላውም እንዲቆም አዘዘ። ከዚያም ሁለቱ አብረው ወደ ውሃው ወረዱ፤ ፊልጶስም ጃንደረባውን አጠመቀው።*

ከእነዚህ ጥቅሶች እንደ ምንረዳው ጥምቀት በራሱ አያድንም፣ ንስሃ መግባትና በእምነት መዳንን ያሳውቃል እንጂ፡፡ አንድ የጌታ ኢየሱስ ተከታይ ስለ ውሃ ጥምቀት አስፈላጊነት ሳይረዳ በመቅረቱ ባለማወቅ ምክንያት ወይም፤ እንድ የታመመ ሰው ጌታን ቢቀበልና፣ ህመሙ ጸንቶበት ለመጠመቅ ጊዜ ሳያገኝ ቢሞት ድነቱን አያሳጣውም፡፡

ነገር ግን አንድ ሰው ጌታን በእምነት መቀበሉን እየተናገረ የውሃ ጥምቀት መፈጸምን ንቆ ቢተወው፣ ወይም ስጠመቅ ሰዎች ካዩኝና በክርስቶስ ኢየሱስ ማመኔን ካወቁ፣ ውጊያ ያስነሱብኛል … ወዘተ በማለት ፈርቶ ሳይጠመቅ ቢቀር ግን የዚህ ሰው መዳን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር የማይቻል ነው የሚሆነው፡፡

*ሉቃ 9፥26፣ "በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል።"*

*ማቴ 10፡32-33፣ "በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፣ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ [33] ነገር ግን በሰው ፊት የሚክደኝን፣ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ።*

3.6) **የውሃ ጥምቀት መጠመቅ፣ ንስሃ ገብቶ፣ በጌታ ኢየሱስ ማመንን በሰዎች ፊት በይፋ መመስከሪያ አንዱ መንገድና ክርስቶስ ኢየሱስን በመከተል ለመኖር የመወሰንን እምነት ማሳያ ነው፡፡**

*ሮሜ 10፡9-10፣ ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ [10] ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።*

*ማቴ 10፡32-33፣ ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ [33] በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።*

3.7) **የውሃ ጥምቀት አንድ ሰው በጌታ ኢየሱስ ካመነ በኋላ አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጽመው ስርዓት ነው እንጂ በየጊዜው የሚደጋገም አይደለም፡፡**

ኤፌ 4፡4-6፣ "በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ [5] አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ [6] ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።"

*3.8) ሐሥ 2፡38-39፣ ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። 39 የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።*

ከዚህ ጥቅስ "የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ" የሚለውን ሐረግ በመያዝ ሕጻናትም መጠመቅ ይችላሉ፣ የሚሉ አሉ፡፡ ነገር ግን እዚያው ጥቂት ዝቅ ብሎ ቁጥር 41 ላይ የሚለውን እንመልከት፡፡

*ሐሥ 2፡40-41፣ "በብዙ ሌላ ቃልም መሰከረና፦ ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ ብሎ መከራቸው። 41 ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤"*

ስለሚል ቃሉን (አምነው) የተቀበሉት ሕጻናትን እንደማይጨምር ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ ሕጻናት አድገው ቃሉን ሰምተው በሰሩት ኃጢአት በመጸጸት ንስሃ መግባት፣ መማር፣ ማመን፣ መወሰንና በአፋቸው መመስከር እስከሚችሉ ድረስ መጠመቅ አይኖርባቸውም፡፡

ከዚህም በላይ ሕጻናት መልካሙንና ክፉውን መለየት፣ ማለትም ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ እስከሚችሉበት ዕድሜ ድረስ ኃጢአት የማይቆጠርባቸው ስለሆነ ንስሃ በመግባት ከኃጢአት መንጻት፣ መጠመቅም አያስፈልጋቸውም፡፡ ዘዳ 1፡39፤ ዮናስ 4፡11፤ ኢሳ 7፡15-16፣ ማቴ 19፡14፡፡

በሐዋሪያት ዘመን ሰዎች በጌታ እንዳመኑ ምንም ያህል ሳይቆዩ ወዲያውኑ ይጠመቁ ነበር፡፡ በአሁኑ ዘመን ብዙ አሳሳች ትምህርቶች የሚታዩ በመሆኑ በርካታ ቤተ-እምነቶች፣ አዳዲስ ሰዎች በጌታ እንዳመኑ ውዲያውኑ ከማጥመቅ ይልቅ፣ ያመኑትን ጊዜ ወስዶ መሰረታዊ የእምነት ትምህርት በማስተማር የወንጌሉ ቃል የተወሰነ ያህል ገብቷቸው እንዳመኑ ሲረጋገጥ እንዲጠመቁ ያደርጋሉ፡፡

**በውሃ ጥምቀት ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች፡** - የጥምቀት ስነ-ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ ተጠማቂዎቹ የሚለብሱት ልብስ በውሃ ሲነከሩ ከሰውነት ጋር ልጥፍ የሚልና የውነትን ቅርጽ የሚያሳይ (transparent) እንዳይሆን በመጠንቀቅ መልኩ ጥቁር ቀለም ያለው ቢሆን ይመረጣል፡፡ ሴቶች የሚለብሱት ረዘም ያለ ቀሚስ በጣም ሰፊ ከሆነ ውሃው ላይ የሚንሳፈፍ እንደይሆን ማስተካከል ተገቢ ነው፡፡ ከተጠመቁ በኋላ ሰውነት ማድረቂያ ፎጣ ነገርና የሚቀይሩት በውሃ ያልረጠበ ልብስ መያዝ፣ ሲጠመቁ የተጠቀሙበት በውሃ የራስ ልብስ መያዣ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

4. **የመከራ ጥምቀት- የጌታ ኢየሱስ (የሐዋሪያቱ) (በተቃዋኒዎች ተቃውሞ፤ በጥላቻና በመከራ/ ውስጥ ማለፍን የሚያመለክት ነው)**

*ሉቃ 12፡49-50፣ በምድር ላይ እሳት ልጥል መጣሁ፥ አሁንም የነደደ ከሆነ ዘንድ ምን እፈልጋለሁ? 50 ነገር ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ፥ እስክትፈጸምም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ?*

*ማቴ 20፡21-22፣ እርሱም፦ ምን ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም፦ እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱም በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለችው። 22 ኢየሱስ ግን መልሶ፦ የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አለ። እንችላለን አሉት።*

በክርስቶስ ኢየሱስ ባመኑና ቃሉን ተከትለው በሚኖሩት ላይ ልዩ ልዩ ውጊያ ተቃውሞና ስደት የመድረሱ ዋናው ምክንያት ተቃዋሚዎች የክርስቶስ ኢየሱስ አስተምህሮና በእርሱ ማመን እንዳይስፋፋ ለመቆጣጠር፣ ቢቻል ለማጥፋት ሲሉ በአማኞችና በወንጌሉ ቃል አገልጋዮች ላይ በሚከፍቱት ውጊያ ነው፡፡ ከዚህ በታች የሰፈሩት ጥቅሶች ይህንኑ ያስረዳሉ፡፡

*ማቴ 5፡11-12፣ "ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣ ቢያሳድዷችሁና ክፉውን ሁሉ በሐሰት*
*ቢያስወሩባችሁ፤ ብፁዓን ናችሁ።[12] በሰማይ የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለ ሆነ ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤት*
*አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንደዚሁ አሳደዋቸዋልና። (2ጢሞ 3፡12)*

*ዮሐ 15፡18-21፣ "ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ።*
*[19] ከዓለም ብትሆኑ ኖሮ፣ ዓለም የራሱ እንደሆኑት አድርጎ በወደዳችሁ ነበር፤ ከዓለም ለይቼ ስለ*
*መረጥኋችሁ የዓለም አይደላችሁም፤ ዓለም የሚጠላችሁም ስለ ዚሁ ነው። [20] 'አገልጋይ ከጌታው*
*አይበልጥም' ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስታውሱ። እኔን አሳደውኝ ከሆነ፣ እናንተንም ያሳድዷችኋል፤*
*ቃሌን ጠብቀው ከሆነም ቃላችሁን ይጠብቃሉ። [21] የላከኝን ስለማያውቁ፣ በስሜ ምክንያት ይህን*
*ያደርጉባችኋል።*

*ዮሐ 16÷33፣ "በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ፣ ይህን ነግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤*
*ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።"*

*1 ጢሞ 4፡1-4፣ በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ*
*ኢየሱስ ፊት፣ መገለጡንና መንግሥቱን በማሰብ ይህን ዐደራ እልሃለሁ፤ [2] ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው*
*ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም።*
*[3] ምክንያቱም ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል፤ ከዚህ ይልቅ*
*ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን፣ የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው*
*በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ። [4] እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ*
*ተረትም ዘወር ይላሉ።*

እንደዚህ ዓይነቱ ተቃውሞና ስደት በአማኞች ላይ የሚደርሰው በተለይ ትክክለኛ የወንጌል አስተምህሮ በአዲስ ሁኔታ በሚጀምርባቸው ወይም ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች ጎልቶ የሚታይ ሲሆን፣ የጌታ ኢየሱስ ተከታዮች በርከት ባሉባቸው አካባቢዎች በተለይም በሰለጠኑ አገሮች ግን አልፎ አልፎ ሊያጋጥም ይችላል፡፡

© ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.